**ቅዱስ ሲኖዶስ**
**The Holy Synod**
**4127 Redwood**
**Oakland, CA 94610**

# በአገራችን በኢትዮጵያ በአማርኛ ተናጋሪ ወገኖቻችን ላይ እየተካሄደ ያለውን የዘር ማጽዳትና ማጥፋት ዘመቻ አስመልክቶ <u>ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የቀረበ ጥሪ</u>

ሚያዚያ ፲፬ ቀን ፪ ሺ ፲ ዓ.ም.

"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።የዋይታና የመራራ ልቅሶ ድምፅ በራማ ተሰማ፤ራሔል ስለ ልጆችዋ አለቀሰች፤የሉምና ስለ ልጆችዋ መጽናናትን እንቢ አለች።" *ኤር 31፥16*

የተወደዳችሁ በአገራችን በኢትዮጵያ እና በመላው ዓለም ተበትናችሁ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን፤

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአምላኳ ጥበቃና በሕዝቧ ፍቅር ነፃነቷንና አንድነቷን ጠብቃ ለብዙ ዘመን ኖራለች። አንድነቷን ከነፃነቷ አስተባብራ የኖረች በመሆኗም ነፃነትን ለሚናፍቁ ሕዝቦች ሁሉ ምልክት ነበረች። በዚህም ምክንያት ለነፃነት የተነሡ ሁሉ ሰንደቅ ዓላማዋን አርማቸው ኢትዮጵያዊነትን አርማቸው አድርገው በነፃነት መንገድ ላይ ተጉዘዋል። እግዚአብሔር አምላክም ለሕዝባችን በሰጠው አርቆ አስተዋይነትም፥ አገሩን የሚከፋፍል ነገር በመካከሉ እንዳይገባና አገራችን በቅኝ ገዢዎች እጅ እንዳትወድቅ ሕዝቡ በአንድነት ቆሞ ኖሮአል። እንግዶችን መቀበል፥ አብሮ መብላት፥ አገር ማልመድ የቆየ ኢትዮጵያዊ ባሕላችን ነው። በዚህ ኢትዮጵያ ባህል ሕዝብ ከሕዝብ ጋር ባህል ከባህል ጋር ተስማምቶ ኢትዮጵያዊ ውበት ያለው ሕብር ፈጥሮአል።

የኢሕአዴግ መንግሥት አገራችንን ኢትዮጵያን በጠመንጃ ኃይል ከተቆጣጠረበት ጊዜ አንሥቶ ግን ይህ የኢትዮጵያ አንድነት ከባድ አደጋ ውስጥ ይገኛል። አገሪቱን በዘርና በጎሣ በመሸንሸን፥ አንዳች ችግር ቢፈጠር በአንድነት አገራዊ መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ እንዲበታተኑ የሚያደርግ የጎሣ ፖለቲካ በሕገ መንግሥቱ ላይ ቀርጾ አስቀምጧል። ይህን ያደረገው የራሱን እድሜ ለማርዘም ነው። በዚሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ የሰብአዊ መብት ጥሰት፤ የመልካም አስተዳደር እጦት እና የኑሮ ውድነት እየጨመረ መምጣቱ የሚታወቅ ነው። የዘር ማጥፋት ዘመቻውንም መልኩን በመቀያየር በቦረናና በአርባ ጉጉ፥ በጋምቤላና በኦጋዴን፥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በአፋር፣ በደቡብ ኢትዮጵያ እና በቤኒሻንጉል በሚኖሩት ወገኖቻችን ላይ በማከናወን ላይ ነው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ይህ እየተከናወነ ያለው የዘር ማጥፋት ዘመቻ ጥቂቶች በብዙዎች ላይ ነግሠው እንዲኖሩ ለማድረግ የታቀደና የኢትዮጵያን አንድነት አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ በመላው ዓለም

ያለን ሕዝቦች የወገኖቻችንን ግፍና ስቃይ ተረድተን ጩኸታችንን በማሰማት ድምጹ ለታፈነበትና በሰቆቃ ላለው ሕዝብ ድምጽ በመሆን በዓለም የተለያዩ መድረኮች ጩኸቱን እንድናደርስለት ጥሪ ታቀርባለች።

በኤርምያስ ዘመን እምባገነን መሪዎች የነበሩ ሲሆን እምነት የሌላቸው እውነት የተለያቸው እግዚአብሔርን የማያከብሩ ሰውን የማይፈሩ ጨካኞች እውነትን የማይወዱ ሥልጣናቸውን ለማቆየት ሲሉ ብቻ እግዚአብሔርን የሚዋሹ ክፉዎች ነበሩ። ከዚህ የተነሳ ሕጻናትን በሥጋና በመንፈስ ይገሉ ነበር። ለዚህ ነበር እግዚአብሔር በኤርምያስ አድሮ ይህን የዋይታ መልዕክት ያስተላለፈው፤ ራሔል የምትወክለው ጠቅላላ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነበር፣ ዋይታዋ ጩኸቷም በግፍ በጨካኞች ስላለቁት የእግዚአብሔር ሕዝብ ሕጻናት ነበር። ምክንያቱም ሕጻናቱ ከፉዎች ስለ ገደሏቸው አልቀዋል የሉም ሞተዋልና ነው።

በክርስቶስ ጊዜ የነበረው ሄሮድስም በደሉን እንደገና ስለደገመው ማቴዎስ ይህንኑ ቃል ተጠቅሟል፤ እኛም ዛሬ እየተጠቀምንበት ነው። ምክንያቱም በሄሮድስም በኤርምያስም ጊዜ የነበሩ መሪዎች ክፉ መንፈስም አሁን በኢትዮጵያ በአሉ መሪዎች ልብ ስለ አለ ነው፤ በአገሪቱ የመንግሥትን ሥልጣን የያዘው አካል በዚያን ወቅት ከነበሩት ሰዎች ጋር አንድ ዓይነት ስለሆነ ያንኑ ጩኸት እንጮኸለን። የኢትዮጵያ ወላጆች አሁን የራሔልን ጮኸት እየጮሁ ነው።

ዛሬ በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ከፍ ብለን ከጠቀስነው ጊዜና ሁኔታ ይበልጥ የከፋ ሁኖ እናገኘዋልን። እናቶች እንባቸው ደርቆ የደም እንባ እያነቡ ይገኛሉ። ይሄው ከፋፋይ መንግስት ተከባብሮና ተፋቅሮ አብሮ የኖረውን ህዝባችንን በሃይማኖትና በዘር ማለትም እስላሙን ከክርስቲያኑ፤ ኦሮሞውን ከአማራው፤ ሱማሌዉን ከኦሮሞው፤ ስልጤውን ከጉራጌ፤ ከንባታ ከወላይታ፤ አፋርን ከኢሳ፤ ሲዳማውን ከጌዶ፤ አኚዋክን ከኑር ፤ ትግሬውን ከቀረው ኢትዮጵያዊ ጋር ለማለያየት ወይም ለመከፋፈል እየሞከረ ነው። ይህ አልበቃ ብሎ አንድ ኢትዮጵያዊ በትውልድ ሀገሩ የመኖርና የዜግነት መብቱ ተነፍጎ አንዱን ዜጋ ከፍ አድረጎ በአንጻሩ ሌላውን ግን እንደ አውሬ በመቁጠር ከሰባዊ ፍጡር አሳንሶ በመመልከት በዜጎች ላይ የሚደረገው የዘር ማጥፋትና ማጥራት ግፍ ሲታይ ከዚህ በላይ ከተጮኸው ጩኸት የበለጠ ያስጮኻል።

የሰለጠነ ፖለቲካ በሚስተናገድበት ባለንበት ክፍለ ዘመን ይቅርና ይቅርና ወደኋላ ተመለሰን በመቶዎቹ በሚቆጠረው ዘመን እንኳን ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ተግባር ነው። አንድን ዜጋ በቋንቋውና በዘሩ ለይቶ ከቦታ እያፈናቀሉ በወገን ስቃይ መደሰት ከየት የተገኘ የፖለቲካ ፍልስፍና ነው? ምን አልባት ከሙሶሎኒ? በፍቅር በአንድነት አብረው የኖሩ ገዳማውያንን በቋነቋ ለይቶ ከገዳም ማሰወጣት፤ የገዳማውያንን መሬት ነጥቆ ለትግሪኛ ተናጋሪዎች ብቻ መስጠት ከደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ ሥርዓት ምን ለየው?

እግዚአብሔር እንዲህ ላሉት የጨካኞች ልብ እንዲህ የሚል መልእክት አለው። “እግዚአብሔር ከሕዝቡ ሽማግሌዎችና ከአለቆቻቸው ጋር ይፋረዳል፤የወይኑን ቦታ የጨረሳችሁ እናንተ ናችሁ፤ ከድሆች የበዘበዛችሁት በቤታችሁ አለ፤ሕዝቤንም ለምን

ታደቅቁአቸዋላችሁ? የድሆችንስ ፊት ለምን ትፈጫላችሁ? ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። ኢሳ3፥13

በመሆኑም ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በአሁኑ ጊዜ እየተካሄደ ያለውን የዘር ማጥፋት ወንጀል፤ የፍትህ እጦት፤ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፤ በሃይማኖት ተቋም ውስጥ የሚያደርግውን ጣልቃ ገብነት እያወገዘ ገዥው ፓርቲ የሀገሪቷን ህገ መንግስት እንዲያከብር እንጠይቃለን። በመጨረሻም ቅዱስ ሲኖዶስ ይህን የህዝቦች ሰቆቃ ለማስቆም ሁሉም የበኩሉን ጥረት ማደረግ እንዳለበት ያምናል። ስለሆነም የሚከተለውን ወገናዊ ጥሪ እናስተላልፋለን።

1. በኢትዮጵያና በመላው ዓለም የምትገኙ የልዩ ልዩ እምነት ተከታይ ወገኖቻችን በዚህ በታላቁ የሕማማትና የትንሣኤ በዓል ጊዜ ክርስቲያን ወገኖቻችን ከቦታቸው ተፈናቅለው መናንያን መነኮሳት ከገዳማቸው ተሰደው በሰቆቃና በእንባ እየታጠቡ የሚገኙበት ጊዜ ነው። ምእመናን፤ ወገኖቻችን ቤታቸው ፈርሶ ንብረታቸው ተወርሶ የመጨረሻው የድህነት እርከን ላይ ደርሰው ልመና እንኳን እንዳይለምኑ መታወቂያ ካርዳቸውን ተቀምተው የቀን ጭለማ ውጧቸው በራሳቸው መንግሥት እየተሰቃዩ ይገኛሉ። ይህንን ግፍ እያዩ ዝም ማለት ከእማኝ ማህበረሰብ አይጠበቅም። ገዥው ፓርቲ ከግፈኝነቱ እንዲታቀብ፤ ወገኖቻችንን በቋንቋና በዘር መለያየቱን እንዲያቆምና መናኝ መነኮሳትን ማሳደዱን እንዲያቆም በአንድነት እንድትነሱ በእግዚአብሔር ስም ጥሪ እናቀርባለን።

2. በአገር ጠባቂ ስም የተቀመጣችሁ የደህንነትና የሠራዊት አባላት በሙሉ፦ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው ሰላም ነው። እናንተ የህዝብ እንጂ የመንግስት አገልጋይ እንዳልሆናችሁ በመገንዘብ ከህዝብ ጎን እንድትቆሙ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪ ያቀርባል።

3. ለኢትዮጵያ ሕዘብ መልካም አስተዳደር ለማምጣት በአማራጭነት የምትታገሉ የፖለቲካና የሰብዓዊ መብት ደርጅቶች በሙሉ፤ አሁን በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ልዩነትን የምታስፋፉበት ጊዜ አይደለም፤ ለዚህ ለልዩነት ያለው የወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት በቂ ነው። አሁን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የሚፈለጉት ከልዩነት የሚያድናቸው ነው። ስለሆነም ልዩነታችሁን ዛሬ ነገ ሳትሉ በአስቸኳይ አስወግዳችሁ በመመካከርና በአንድነት ኢትዮጵያና ህዝቧን ከጥፋት ለማዳን ትደርሱ ዘንድ በእግዚአብሔርና ከጥፋት ጎዳና ላይ በምትገኘው አገራችን በመከራ ላይ ባለው ሕዝባችን ስም አፋጣኝ መልስ የሚሻ ጥሪ እናቀርባለን።

4. **በመጨረሻም ሁሉም ነገር የሚከናውነው በእግዚአብሔር ጊዜ መሆኑን እናውቃለን። በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በተለያየ ምክንያት በቡድን፤ በግል፤ በቤተሰብም ሆነ በድርጅት የተቀያየማችሁ ወገኖች አንድነታችን እጅግ የሚያስፈልግበት ወቅት በመሆኑ በዚህ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሕማምና መከራ በምናስብበት የሕማማት ሳምንት ይቅር እንድትባባሉ የፍቅር ባለቤት በሆነው አምላክና የግፍ ሰለባ በሆነው ህዝባችን ስም ጥሪ እናቀርብላችኋለን።**

**በመጨረሻም ቅዱስ ሲኖዶሱ ሰሙነ ሕማማቱን በሰላም እንዲያስፈጽመን ለብርሃነ ትንሣኤውም እንዲያደርሰን በጸሎት አምላካችንን ይለምናል።**

***በስደት የሚገኘው ሕጋዊው ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን***
***ቅዱስ ሲኖዶስ***
***ኦክላንድ ካሊፎርኒያ***